ኤፕሪል 21፣ 2023

ውድ የ Montclair የአካዳሚክ እና ማበልፀጊያ ትምህርት ቤት ማኅበረሰብ፣

Mr. Daniel Barks ለ2023-2024 የትምህርት ዘመን እና ከዚያ በኋላ ላሉት ጊዜያት ቀጣዩ የ Montclair የአካዳሚክ እና የማበልጸጊያ ት/ቤት መሪ ተደርገው መመረጣቸውን ስንገልጽልዎ በደስታ ነው። Mr. Barks የMontclairን ብዙ ጥንካሬዎች በመገንባታቸው እንደሚቀጥሉ እና የMontclairን የተማሪዎች ስኬት መሰረት እንደሚያከናውኑና እንደሚያስፋፉ እንተማመንባቸዋለን።

በግለ ታሪካቸው ላይ እንደተገለጸው Mr. Barks በ Denver Public School በመስራት ከ12 ዓመታት በላይ የስራ ልምድ ያላቸው ከመሆኑም በተጨማሪ የማስተማር ጉዟቸውን የጀመሩት በMontclair የአካዳሚክ እና የማበልጸጊያ ት/ቤት ነበር! ግለሰቡ በመላው ዲስትሪክቱ ውስጥ በሚገኙ አንደኛና መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የክፍል መምህርነትን፣ የመመሪያ አሰጣጥ አሰልጣኝነትን፣ የፕሮግራም ስራ አስኪያጅነትን፣ ረዳት ርዕሰ መምህርነትና ዋና ርዕሰ መምህርነትን ጨምሮ በተለያዩ የስራ ድርሻዎች ላይ አገልግለዋል። በ Marie L. Greenwood የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት ውስጥ በቅርቡ ከነበረው የነዋሪ ርዕሰ መምህ ሚናው በተጨማሪ፣ Mr. Barks ከብዙ ቋንቋ ተማሪዎች ጋር የሚሰሩ አስተማሪዎችን ለምርጥ ልምምዶች ለማሰልጠን እና ለመደገፍ ለ Denver Public Schools በብዙ ቋንቋ የሚሰጥ ትምህርት መምሪያ ሰርቷል። Mr. Barks ወደ Montclair በመመለሳቸው እጅግ ደስተኞች ነን!

የ Montclair የትምህርት ቤት አማካሪ ኮሚቴ (SAC) ለቀጣዩ የMontclair መሪ ከማህበረሰቡ በተገኘው ግብዓት ላይ ተመስርቶ ቁልፍ መግለጫ ያዘጋጀ ሲሆን የስራ ልማደቸውና ጥንካሬዎቻቸው ከዚህ መግለጫ ጋር የሚጣጣም ብዙ የመጨረሻ እጩዎችን ማግኘት ችለን ስለነበር እድለኞች ነን። በተለይም Mr. Barks brings ሰፊ ለመምህራን ቡድኖች ድጋፍ የማድረግና የማገልገል ልምድ፣ ጠንካራ የመመሪያ አሰጣጥ አመራርነት፣ ንቁና ወጥ የግንኙነት ክህሎቶች፣ ከብዙ ቋንቋ ተማሪዎች ጋር የመስራት ልምድ፣ በሁሉም ህጻናት ላይ ያተኮረ እኩልነት ተኮር ትኩረት ከማቅረባቸውም በተጨማሪ ሁሉንም ባለድርሻ አካላት አካሳች፣ አሳታፊና ፍትሀዊ ትምህርት ቤቶችን የመገንባት ዝግጅት ላይ የማሳተፍ ታሪክ ያላቸው ሲሆን ይህም ማህበረሰቡ ለቀጣዩ መሪ ከዘረዘራቸው ጥቂት ወሳኝ ባህሪያት መካከል አንዱ ነው።

በዚህ አጋጣሚ ሁሉንም ሰው ግብአትና ግብረ መልስ በመስጠት ስላበረከተው አስተዋጽኦ ለማመስገን እንወዳለን። እርስዎ በሂደቱ ላይ ቀደም ብለው ያካፈሉን ግብዓት በትምህርት ቤት አማካሪ ኮሚቴው (SAC) የእጩ መግለጫና የቃለ መጠይቅ ጥያቄዎችን ለማዘጋጀት ጥቅም ላይ ውሏል። በማህበረሰብ መድረክና ለእጩ ቪዲዮዎች ምላሽ የሰጡን ግብረ መልስ ከመጨረሻ ቃለ መጠይቁ በፊት የበላይ ተቆጣጣሪው ተገልጿል። እርስዎንም ሆነ የትምህርት ቤት አማካሪ ኮሚቴውን (SAC) ለቁርጠኝነታችሁና የሂደቱ አጠቃላይ አካል ስለነበራችሁ በእጅጉ እናመሰግናችኋለን። ኮሚቴው የትምህርት ቤት ማህበረሰቡን በጥሩ ሁኔታ ከማገልገሉም በተጨማሪ ለMontclair ቀጣይነት ያለው ስኬት ያላቸውን የማያወላውል ቁርጠኝነት በእያንዳንዱ አቅጣጫ አሳይተዋል።

እባክዎ ስለ Mr. Barks በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ይመልከቱ፣ ነገር ግን ለአሁኑ Mr. Daniel Barksን ቀጣዩ የMontclair የአካዳሚክ እና የማበልጸጊያ ት/ቤት መሪ አድርገን ለመቀበል በምናደርገው የእንኳን ደህና መጡ አቀባበል ላይ ይቀላቀሉን!

ከሰላምታ ጋር፣

Dr. Dana Williams
የትብብር ዳይሬክተር፣ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ትብብር 3

Scott Wolf
የክወና አገልግሎቶች ዳይሬክተር